# አገልግሎትና የአገልግሎት ውጤታማነት

## OAKLAND, CA 2018

- አገልግሎታችን ውጤታማ እንዲሆን አስቀድመን የአገልግሎትን ምንነትና መሰረቱን ማወቅና መለየት መቻል አለብን፡፡
- አገልግሎት ከሌሎች ስራዎች በተለየ በእግዚአብሄር ምርጫና ጥሪ የሚያዝ ስፍራ ነው ፡፡ አገልጋይንም ለስራው የሚጠራና የሚያሰማራው የስራው ባለቤት የሆነው ህያው እግዚአብሄር ነው፡፡
- አገልግሎት ማለት ፡- በግሪክ ዲያኮናይ \diaconay\ ይባላል፡፡ ዲያኮናይ አንድ ወጥ ትርጉም የለውም ፡፡ ነገር ግን በውስጡ **የተለያዩ እምቅ ትርጉሞችን ይዞ ይገኛል**፡፡

# 1. አገልግሎት እድል ነው

- አገልግሎት የሰማይና የምድር ጌታ የሆነውን ታላቁን እግዚአብሄርን ለማገልገል የሚሰጥ እድል ነው፡፡ መፅሃፍ ቅዱስም እግዚአብሄርን ማገልገል እድል እንደሆነ ይናገራል፡፡

ሐዋ 1፤16-17

- በብሉይ ኪዳን ብንመለከትም አገልግሎት በእግዚአብሄር ምርጫና እግዚአብሄር እንዲያገለግሎት እድል በሰጣቸው ሰዎች ብቻ የሚከናወን ስራ ነበር፡፡ ንጉስ ዳዊትም ይህንን የአገልግሎት ምንነት በመረዳቱ የቃል ኪዳን ታቦቱን ይሸከሙ ዘንድ እግዚአብሄር ከመረጣቸውና እድሉን ከሰጣቸው ውጭ ማንም እንዳይነካ ደጋግሞ ይናገር ነበር፡፡ 1 ዜና 15፤2

- ስለዚህ ሁልጊዜም እግዚአብሄርን ልናገለግል ስንነሳ ከምድር ላይ ካሉት ህዝቦች በሙሉ በመለየት እግዚአብሄርን እናገለግለው ዘንድ እድሉን እንዳገኘን ማሰብና መቁጠር አለብን፡፡ ለአገልግሎት ስንነሳም እራሳችንን ትልቅ እጣ እንደወጣለት እድለኛ ሰው መቁጠርና ማየት አለብን፡፡ ዘሁል 16፤9 ዕብ 5፤1
- በዚህ መንፈስ ስናገለግለው እርሱን በማገልገል ውስጥ ያለውን እድል ፈንታ እናገኛለን ፡፡ እርሱ ለአገልጋዮቹ ባዘጋጀው የከፍታ፣ የክብርና፣ የሃይል ስልጣን ውስጥ ያስገባናል፡፡ ዘሌ 7፡35

# 2. አገልግሎት ስራ ነው

- እኛ የእግዚአብሄር አገልጋይ ነን፣ እርሱን አገለግላለሁ ብለን ስንናገር እግዚአብሄር ደግሞ የእኔ ሰራተኛዬ ነው ብሎ እንደ ሰራተኛ ይቆጥረናል፡፡ ከዚህ የተነሳ እግዚአብሄር ከሰራተኞቹ ትጋትን፣ መስጠትንና ታማኝነትን ይፈልጋል፡፡ **ኤር 48፡10**
- አገልግሎት ስራ በመሆኑ በውስጡ አሰራርን፣ ተጠያቂነትን፣ አለቃን አካቶ ይዟል ፡፡ በመሆኑም ይህንን የእግዚአብሄር ስራ እንደ አሰራሩ በተጠያቂነት መንፈስ በትጋት መሰረት ይገባናል፡፡ **፣ ቆሮ 16፡15-16**
- አገልግሎት ስራ እንደሆነ ስንረዳ ሳንታክት ለማገልገል ሃይልና ብርታትና ይሰጠናል፡፡ አገልግሎት እንዳለን ስናውቅም በእኛ የሚሰራ ስራ እንዳለ ስለምናውቅ ሳንታክት ለመስራት ብርታት ይሆንልናል **2ቆሮ 4፡1**

# 3.አገልግሎት ውጊያ ነው

- የምንዋጋውም የንጉሳችንን የእግዚአብሄርን የልብ ፈቃድ ለመፈፀም በሚፈልግ የቁርጠኝነት ልብና መንፈስ ነው፡፡ አገልጋይ ነን ስንልም ጠላት በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ሊሸምቅብን እንደሚመጣ መረዳት አለብን፡፡
- አገልግሎት ውጊያ መሆኑን የተረዳው ሃዋሪያው ጳውሎስ ሁልጊዜም በአገልግሎት ውስጥ መፈተን እንዳለና ያንንም በድል መወጣት እንደሚገባ ይናገራል፡፡ ፊሊ 2፤22
- ከጌታ ስራ የተነሳ ሁልጊዜም ለውጊያ እራሳችንን ማቅረብ ይገባናል፡፡ ለራሳችን ነገር ከምንዋጋው በላይ ለመንግስቱ መስፋት፣ ለመንግስቱ ጉዳይ የምንዋጋው ቀዳሚ ነገር ነው፡፡

# የውጊያ ክልሎቻችን

1. ከከፋት መናፍስት አለም
2. ከራስ ማንነት ጋር
3. ከራስ ሰዎች ጋር (ቤተሰብ፣ ወንድሞች ወዘተ)
4. ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር

# <u>4. አገልግሎት አምልኮ ነው</u>

- አገልግሎት አምልኮ ነው ፡፡ አምልኮ ደግሞ ለእግዚአብሄር ብቻ የሚሰጥ ነው ፡፡ አገልግሎትም በእግዚአብሄር ብቻ የሚሰራ ስራ ስለሆነ እውነተኛና ትክክለኛ አምልኮ ነው ፡፡ ስለዚህ ጌታን ስናገለግለው እውነተኛ አምልኮ እየሰጠነውና እያመለክነው እንደሆነ ማሰብና መረዳት ተገቢ ይሆናል፡፡ ቆላ 3፥24 ያዕቆብ 1፥27
- **አገልግሎት** ፡- ለእግዚአብሄር ያለንን ፍቅር ፣ ለእግዚአብሄር ያለንን መውደድ የምንገልጥበት መድረክ ነው፡፡ **ኢሳ 56፥6**

# ውጤታማ አገልግሎት ማለት ምን ማለት ነው?

- አንድ ሰው ውጤታማ የሆነ አገልግሎት አገለገለ የሚባለው በአገልግሎቱ ምን ማድረግ ሲችል ነው፡፡
  **1. ሰዎች በፈቃደኝነትና በደስታ ለእግዚአብሄር ክብር እንዲገዙ ማድረግ ሲቻል ነው።** መሳ 5፡2
- ሰዎች ለተገለጠው የእግዚአብሄር ነገር፣ ለተገለጠው የእግዚአብሄር ፍቃድ እልል ብለው በደስታ ለዚያ ነገር ሲሰጡ ብቻ ውጤታማ አገልግሎት አገለገልን ይባላል፡፡
- ሰዎች አድንቀው ፣ አጨብጭበውና ተገርመው ብቻ ከሄዱ ይህ የውጤታማ አገልግሎት መገለጫ አይደለም፡፡
- ውጤታማ አገልግሎት ፡- ሰውን ለማዝናናት፣ ለማሳቅና በመኮርኮም ላይ የተመሰረተ አይደለም፡፡
- ሰዎች በፈቃደኝነትና በደስታ ለእግዚአብሄር ነገር ወድቀው እንዲሰግዱ ማስደረግ የውጤታማ አገልግሎት መገለጫ ነው፡፡ **ዘሌ 9፡23-24**

- ፀሎታችን፣ ትምህርታችን፣ስብከታችን ሁሉ ህዝቡ በፈቃዱና በደስታ ለተገለጠው የእግዚአብሄር ነገር እንዲገዛ ማድረግ ነው፡፡
- ህዝብን ለተገለጠው የእግዚአብሄር ቃልና ሃሳብ እንዲገዛ ካላደረግን አገልግሎታችን ውጤታማ መሆን አልጀመረም ማለት ነው፡፡

# 2. ከሰፈር ወደ ዮርዳኖስ ህዝቡን ለማንቀሳቀስ ነው

ኢያሱ 3፤3

- የአገልግሎት ውጤታማነት የሚገለጥበት ሌላው መንገድ ሰዎች ከለመዱትና ከተቀመጡበት ነገር አስነስቶ ወደ እግዚአብሄር ነገር ማንቀሳቀስና ማስከተል መቻል ነው፡፡
- ህዝቡ ታቦቱን የተሸከሙትን ሌዋውያን ካህናትን የተከተሉት ወደ ሞላው ዮርዳኖስ እንጂ ወደ ገላጣና የተመቸ ሜዳ አልነበረም፡፡
- ሰዎችን ከተቀመጡበት ስፍራቸው አስነስቶ ዋጋ (ማቴ 21፥7) ወደሚያስከፍል ወደ አዲስ ነገር ማድረስና ማንቀሳቀስ ነው፡፡

- ህዝቡን ከሰፈሩ አስነስቶ (ዋስትና ካለውና ከተመቸው ነገር) ወደ እግዚአብሄር ነገር ማድረስና ማስከተት ይህ የአገልግሎት ውጤታማነት ነው፡፡ ዘኁ 10፡1-2
- መለከቱን መንፋት እንደተነፋለት ዓላማም ህዝቡን ለሰልፍ ማስከተትና ማንቀሳቀስ ይህ የውጤታማ አገልግሎት መለኪያ ነው፡፡
- መለከቱን ካህናት ሲነፉ ህዝቡ በፈቃዱ ድንኳኑን ነቅሎ ከሰፈሩ በመነሳት ለሞትና ለውጊያ ይታዘዛቸው ነበር፡፡

# ታዲያ የውጤታማ አገልግሎት መሰረቱ ምንድን ነው

- ኢየሱስ ታላላቅ ተአምራት ያደርግ ነበር፡፡ እውር ያበራል፤ ሽባ ይተረትራል፤ የሞተ ያስነሳል፤ የጐበጠ ያቀናል፡፡
- የእግዚአብሄርን የጊዜው ፈቃድ ያማከለ ልዩ ትምህርት ይገልጣል ፡፡ ለሚማረው ህዝብ ይመግባል፡፡
- ይህ ሁሉ ሆኖ ግን በኢየሱስ አገልግሎት አባል የነበረው 120 ሰው ብቻ ነበር፡፡ በእነዚህ 120 ሰዎች እውነተኛ እሳት ወደቀ፡፡ አለምን ገለበጡ፡፡
- የመጀመሪያዋ ዘመን ቤተክርስቲያን በዚህ የአገልግሎት ውጤታማነት ላይ ትኩረት ስለሰጠች ያመጣችው ተፅዕኖ እኛ ሁለት ሺህ አመት ከሰራነውና ካመጣነው የበለጠና የበዛ ነው፡፡

# 1.ገብቶ መውጣት

- **ዘሌ 9፡23-24**
- የሙሴና የአሮን አገልግሎት ውጤታማነት የተያያዘው ከሁሉም ነገር በፊት ወደ መገናኛው ድንኳን ገብተው መውጣታቸው ነበር፡፡
- ህዝቡን ለማስተማር ፣ ለመባረክ፣ ለመስበክ ከመሄዳቸው በፊት መጀመሪያ ወደ እግዚአብሄር ድንኳን ገብተው ወጡ፡፡
- ሙሴና አሮን የሚያገለግሉት በድንገትና በእግር መንገድ ሳይሆን አስቀድመው የድንኳን ህይወት ውስጥ ገብተው በመውጣት ነበር፡፡
- ሙሴ በበትር ታላላቅን ተአምራት እንዲሰራ ብቃት የተሰጠው ሰው ነበር፡፡ ህዝቡን ነፃ እንዲያወጣ ወደ ፈርኦን የተላከ ሰው ነበር፡፡
- ይህ ሁሉ ብቃት ቢኖረውም አገልግሎቱ በሰሚዎች ዘንድ ጆሮ እንዲያገኝ እግዚአብሄር በከባድ ደመና እመጣልሃለሁ አለው፡፡
- ዘፀ 19፡9 **ዘፀ 33፡9-10**

# ወደ ድንኳን ገብተን ስንወጣ በአገልግሎታችን ምን ይሆናል?

## 1. ድምፅን ይዘን እንወጣለን

- ወደ ድንኳን ገብቶ የሚወጣ አገልጋይ ትምህርትና ስብከት ብቻ ሳይሆን ድምፅ ይዞ ይመጣል፡፡
- ድምፅ ፡- ሃይል ይሆናል፣ መለኮታዊ ጉልበት ይሆናል፡፡
- ድምፅ ፡- ምሪት ይሆናል
- ድምፅ ፡- ህዝብን ካለበት ስፍራ ወደሚቀጥለው ለማሰጓዝ ድፍረት ይሆናል፡፡
- ጴጥሮስ ስለ አገልግሎቱ ውጤታማነትና መለወጥ ሲናገር ምክንያቱ ከጌታ ጋር በተራራ ላይ አብረን በቆየንበት ሰዓት ከሰማይ ድምፅ ሲወርድ መስማታችን ነው እያለ ይናገር ነበር፡፡ 2ጴጥ 1፡16-19

# 2. ንፅህና ይዘን እንወጣለን

- በብሉይ ኪዳን እግዚአብሄርን የሚያገለግሉ ካህናት ወደ እግዚአብሄር መቅደስ ሲገቡ ታጥበውና ከቆሻሻ ነፅተው ይገቡ ነበር፡፡ ሮሜ 10፡15
- መታጠብ በምናገለግለው ህዝብ ዘንድ ተአማኒነትን ይሰጠናል ፡፡
- የእኛም ህይወት በጥራት እንዲሞላ መጀመሪያ ወደ ድንኳኑ ገብተን በቃሉና በደሙ ታጥበን መውጣት ይገባናል፡፡ 1ዮሃ 1፡7
- አገልጋይ ካለበት መንፈሳዊ ስፍራ የተነሳ ጥቃቅን የምትባለው ድካሙ ሁሉ በህዝቡ ዘንድ የተገለጠና የሚታወቅ ነው፡፡
- እግዚአብሄር ደግሞ ካህንን ከመላዕክት ሳይሆን ከሰው መርጦ ነው የሚቀባው ፡፡ ሰው ደግሞ ሊሳሳት ይችላልና አስቀድመን ገብተን በደሙ መንፃትና መታጠብ አለብን፡፡

- ኤልያስም አንደኛው ሰው ነበር፡፡ በአንድ ወቅት ከሰማይ እሳት አወረደ፡፡ እዛው ምዕራፍ ላይ ተኛ ፤ደከመ፤ ተስፋ ቆረጠ፡፡
- ጌታ ግን እንደገና አበርትቶ ፀጋውን አካፍሎ በእሳት ፈረስና ሰረገላ ላይ ቁጭ ብሎ ወደ ላይ ወሰደው፡፡
- ዛሬም እግዚአብሄር የሰጠንን ነገር አካፍለን ወደ ሌላ ከፍታ እንድንሄድ ወደ ድንኳኑ እንግባና እግራችንን እንታጠብ፡፡ ህይወታችን በደሙ ይንፃ፡፡ **ህዝ 34፡18-19**
- እዚህ ክፍል ላይ እንደምናየው ውሃው ጥሩ ነው፡፡ ነገር ግን ከጠራ ውሃ ጠጥተው እንዳይረኩ ግን እግራቸው አደፈረሰው፡፡
- የያዝነው ቃልና መልዕክት ጥሩ ቢሆንም ነገር ግን የእግራችን \የህይወታችን\ ጥራት በአግባቡ ሰዎች እንዳይጠጡት ሊያደፈርስ ይችላልና ወደ ውስጥ ገብተን በደሙ ታጥበን እንውጣ፡፡

# 3. ማብረቅረቅ ይሆናል

- **ዘፀ 34፡29**
- ሙሴ ከእግዚአብሄር ጋር ተገናኝቶ ፣ ከእግዚአብሄር ጋር ጊዜ ወስዶና ተነጋግሮ ሲመጣ መለኮታዊ ብርሃን በራሱ ላይ መጣ፡፡
- በእርሱ ያለው የእግዚአብሄር ክብር በሩቅ መታየት ጀመረ፡፡ የክብሩ ፀዳል ታየበት፡፡
- ዛሬም ነቃፊ፣ ተቺ፣ አጉረምራሚ ህዝብ በበዛበት መካከል የእግዚአብሄርን ስራ ለመስራት መጀመሪያ ከእነርሱ በተለየ ማብራትና ማብረቅረቅ ይጠበቅብናል፡፡
- እንኳን ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋግረን አይደለም ሳኦል ከሳሙኤል ጋር ተነጋግሮ ሲመለስ “ የቂስን ልጅ ምን አገኘው “ የሚያስብል ነገር በህይወቱ ተከስቷል፡፡
- የእግዚአብሄርን ነገር በቸልተኝነትና እንደ ሁለተኛ ነገር ማየት የለብንም፡፡ ቅድሚያ ስንሰጠው ሁሉ ነገራችን ቅድሚያ ያገኛል፡፡

# 4. በእግዚአብሄር ፊት ማረፍና መናገር ይሆንልናል

- **2ሳሙ 7፡18**
- ገብቶ የሚወጣ አገልጋይ እስከ ግል ችግሩና ጉዳዩ የሚወጣ አይሆንም፡፡ ነገር ግን ችግሩንና ያለበትን ነገር በእግዚአብሄር ፊት ተነግሮ ይወጣል፡፡ ድምፁን ለእግዚአብሄር ያሰማል፡፡
- ብሶታችንን፣ ልመናችንን፣ጥያቄያችንን፣ በልባችን ያለውን ሁሉ በእግዚአብሄር ፊት አዲስ ተናግረን ልባችንን አሳርፈን እንውጣ፡፡
- እኛ ስናርፍ በአገልግሎታችን ብዙዎችን እናሳርፋለን ፡፡
- ለምሳሌ ፡- በትዳር፣ በፋይናንስ፣ አገልግሎት ወዘተ ችግር አለ፡፡
- ለማባረር ደግሞ እንደ ዳዊት መግባትን ዛሬ መልመድ አለብን፡፡
- ገብተን ስናርፍ – ህዝቡን እናሳርፋለን፡፡
- ለማረፍ ደግሞ በእግዚአብሄር ፊት ገብተን እንናገር፡፡

# ወደ ድንኳን እንዴት እንገባለን?

## ፤.በእግዚአብሄር መጥራት ይጀምራል

ዘፀ 19፡20-21

- ሙሴ ወደ ተራራው የወጣው በራሱ ተነሳሽነት ብቻ ሳይሆን በአግዚአብሄር ጥሪ ነበር፡፡
- በድንኳን ህይወታችን መታደሰም የመጀመሪያው የእግዚአብሄር ጥሪ ነው፡፡
- በእኛ ውስጥ መፈለግንና ማድረግን የሚያመጣው እርሱ እግዚአብሄር ነው፡፡

መዝ \43\፡3-4

- ዳዊት በእግዚአብሄር ሃይል ወደ እግዚአብሄር ህልውና እንደገባ ቃሉ ይነግረናል ።

**መዝ\71\፡16** - በእግዚአብሄር ሃይል እገባለሁ።

- ምንም አይነት የስጋ ድካም ፣ ምንም አይነት የክፋት መሰናከል እንዳያግደን እግዚአብሄር ሃይሉን ይልክልናል ። በሃይሉ እንገባለን።
- የእግዚአብሄር ሃይል የክፋትን ስራና አሰራር መትቶ ወደ ህልውናው ሙላት ያስገባናል።
- በእኛና በእግዚአብሄር መካከል የገባ ማናቸውም ገደብ ዛሬ ይሰበራል።

# 2. መጠማትን መፍጠር

- እግዚአብሄርን መጠማትና እግዚአብሄርን መናፈቅ ወደ ድንኳኑ ለመግባት ሌላኛው መርህ ነው፡፡
- እግዚአብሄር ቢጠራንም ጥማት ከሌለን በአግባቡ ለመፈፀም እንቸገራለን፡፡ ስለዚህ ዛሬ እግዚአብሄር ይህንን ጥማት በውስጥ ይፈጥርብናል፡፡ **መዝ\63\፡1-2**
- ዳዊት በምድረ በዳ ፣ የእግዚአብሄርን ክብርና ሃይል ያይ ዘንድ በከፍተኛ ሁኔታ ጥማት እንደተፈጠረበት ይናገራል፡፡
- **መዝ \42\፡1-2** - ዛሬ የአምላኬን ፊት ለማየት ጓጓሁ፣ ናፈቅሁ እንል ዘንድ እግዚአብሄር በውስጣችን ከእርሱ ህልውና ጋር ህብረትን የሚፈልግ ጥማት ይሰጠናል፡፡

# ታዲያ ጥማት እንዴት ይፈጠርብናል?

## ሀ. ከክብር በመውረድ  ኤር 48፡18

- ጥማት እንዲፈጠርብን መጀመሪያ ክብሬ ከምንለው ነገር መውረድ አለብን፡፡
- የእኛ የምንለውን ስሜት፣ ስምና ማንነት ጥለን ዝቅ ማለት አለብን፡፡
- ክብራችንን ስንጥል ጥማት ይፈጠርብናል ፡፡ ጥማት ሲፈጠርብን ደግሞ ወደ እግዚአብሄር ህልውና ውስጥ መግባት ይሆንልናል፡፡
- ጳውሎስ ከፈረሱ ላይ ወደቀ ፡፡ ሲነሳ ግን ጥማት ተፈጥሮበት ፣ ወደ እግዚአብሄር ህልውና የመግባት ልዩ ፍላጐት ተሞልቶበት ተመለሰ፡፡

# ለ. ማሰብና ማሰላሰ መዝ \143\፡5-6

- ዳዊት የእግዚአብሄርን የቀድሞ ዘመን እና ስራ አሰበ፡፡ ይህን ማድረጉ ደግሞ ጥማትን በውስጡ አቀጣጠለበት፡፡
- እኛም የአባቶቻችን አምላክ እግዚአብሄር በነሙሴ ፤በነኢያሱ፤ በነኤልያስ የሰራውን ስናስብና ስናሰላስል ጥማት ይፈጥርብናል፡፡
- ሙታንን ያስነሳ፤ ድውያንን የፈወሰ፤ ህዝቡን ያሻገረ፤ በድል የመራ፤ ክብሩን የገለጠ እግዚአብሄርን ስናሰላስል ልዩ ጥማት በውስጣችን ይፈጠርብናል፡፡
- ዳዊት የተቀመጠው ቤተ መንግስት ነበር ፡፡ ሁሉ በዙሪያው ቢኖርም የእግዚአብሄርን ስራ በማሰላሰሉ ውስጡ ከተፈጠረው ነገር የተነሳ ተጠማሁ ማለት ጀመረ፡፡
- ቤተመንግስቱን ምድረበደ የሚያስመስል የጥማት መንፈስ ዛሬ ይፈጠርብናል፡፡
- ጥሩ አገልጋይ ነኝ ፤ ደርሼያለሁ፤ እንዳንል የሚያደርግ መንፈስ ዛሬ ይወርድብናል፡፡

# 3. ፍፁም የተሰጠ ዋጋን መክፈል

**መዝ \66\ ፡13-14**

- እግዚአብሄርን ለመገናኘት በመጀመሪያ የሚቃጠል መስዋዕት ያስፈልገናል፡፡
- እግዚአብሄር ቀን፣ ሌሊት፣ በማይመች ሰዓትና ጊዜ ሊጠራን ይችላል፡፡ ያን ጊዜ ሁሉን ትተን እንድንከተለውና እንድንታዘዘው የመስዋዕትነት መንፈስ ሊኖረን ይገባል፡፡
- እግዚአብሄር ይጥራን እንጂ ያንን መልስ ለመስጠት ዋጋን መክፈል አለብን ፡፡ ፍፁም የተሰጠ ዋጋ መክፈል አለብን፡፡ **ዘፀ 29፡42**
- በሙሉ ዋጋ በእግዚአብሄር ጥሪ መልስ መስጠት እርሱ ልዩ ጥማትን በውስጣችን ይፈጥራል፡፡

# 4. ከሰፈር መውጣት

- **ዘፀ 19፡17** - ሙሴም ህዝቡን ከእግዚአብሄር ጋር ለማገናኘት ከሰፈር አወጣቸው፡፡
- በሰፈር ሆነን ወደ እግዚአብሄር ህልውና መግባት አንችልም
- **ዘፀ 33፡7**
- ዛሬ ከሰፈር መውጣትና ወደ ህልውናው መግባት አለብን ፡፡

**ከሰፈር መውጣት ማለት**

1. ከብዙሃኑ አስተሳሰብ ተፅእኖ ነፃ መውጣት

- ብዙውን ለመምሰል አለመሞከር

2. የልብ ንፅህናን መያዝ

- **መዝ \106\፡16** - ሙሴና አሮንን በሰፈር ተመቀኙአቸው ፡፡

# 5. እምነት

- የህይወት አቋም
- የህይወት ዲስፕሊን ይዞ መገኘት